# “የአስመራው ንጉስ” አጣሪ ቡድኑን ምን እያሉት ነው?

ጀማል አብደላ abedelaj@yahoo.com

“… በአደባባይ ዕርቃኑን ወጥቷል፡፡ ሆኖም ዕርቃኑን መሆኑን የተገነዘበው አይመስልም ወይም ሊገነዘበው አይፈልግም–የኤርትራው የአንድ ሰው አገዛዝ…” ይላል ከመሰንበቻው አይጋ ፎረም በተሰኘው ድረ-ገጽ ላይ አቶ ዘርዑ ሐጎስ በተባሉ ኢትዮጵያዊ የቀረበው ጽሑፍ፡፡ በእርግጥ ፀሐፊው በተባ ብዕራቸው የአስመራውን አምባገነናዊ አገዛዝ የኪሳራውን መነሻ እየነቀሱ ተገቢና ትምህርት ሰጪ በሆነ ሁኔታ ቃኝታውታል፡፡ የውድቀቱን ምክንያቶች ከነባራዊ ዕውነታው ጋር እያያያዙም፤ በዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ፊት በውሸት ዲስኩር ተጀቡኖ ራቁቱን መቆሙን በማያሻማ ቋንቋ ነግረውታል፡፡

ዳሩ ግን ምን ያደርጋል?! - የእኚህን ሀገር ወዳድ ዜጋም ይሁን ዓለም አቀፉን ማህብረሰብ ጨምሮ የሌሎች ሠላም ወዳድ ኃይሎችን “የሠላም ያለህ!” ጩኸትና ተግሳፅን መስማት ለተሳነው ሰው የተነገረ ይመስል፤ የአስመራው አስተዳደር ‘ጆሮ ዳባ ልበስ’ ማለትን ስራዬ ብሎ ተያይዞታል፡፡ ታዲያ ለዚህ አባባሌ ሩቅ መሄድ የሚያሻኝ አይመስለኝም፡፡ ምክንያቱም ሰሞኑን በመንግስታቱ ድርጅት የጸጥታው ምክር ቤት በ13 ድጋፍና በሁለት ድምፀ ተዓቅቦ የጣለበትን ሁለተኛ ማዕቀብን ተከትሎ፣ የሶማሊያንና የኤርትራን ጉዳይ እንዲያጣራ የፀጥታው ምክር ቤት የሰየመውን አጣሪ ቡድንን፤ “ሙያዊ ክሂሎት የሌለው፣ በፈጠራ የተሞላ ሪፖርት ያቀረበ ወዘተ” እንዲሁም ሪፖርቱን “የአሜሪካንና የኢትዮጵያን መንግስታት ፍላጎት ለማሟላት የቀረበ” የሚል “ከአፈርኩ አይመልሰኝ” አስገራሚ ምላሹን መጥቀስ ስለሚቻል ነው፡፡

እርግጥ ይህን የአስመራውን መንግስት “የበሰበሰ ዝናብ አይፈራም” ዓይነት ሁሉንም ነገር የማጣጣል አባዜ የተጠናወተው ግትር ፖለቲካ አይሉት እንካ ሰላንቲያን በአይጋ ድረ-ገጽ ላይ “የመንግስታቱ ድርጅት ‘ውሸት’ የጻፈብኝን አጣሪ ቡድን ይቀይርልኝ”

የሚል የስሞታ ደብዳቤን የተመለከተ ሰው፤ እንደ እኔ በግርምት ብዕሩን ከወረቀቱ ጋር ማገናኘቱ አይቀርም፡፡

እናም በዚህ ጽሑፌ "የተባበሩት መንግስታት ድርጅት (ተመድ) የሰየመው አጣሪ ቡድን እነ አቶ ኢሳያስ የሰጡትን 'የዳቦ ስም' የያዘ ነውን?'፣ እውን በሻዕቢያ ላይ የተጣለው ሁለተኛው ማዕቀብስ የሌሎች ወገኖችን ፍላጎት ለማሟላት ነውን?' የሚሉ ጥያቄዎችን በማንሳት ዕውነታውን ከኤርትራ ህዝብ መፃኢ ህይወት አኳያ ጋር በማስተሳሰር ለውድ አንባቢዎች እንዲህ አቅርቤዋለሁ፡፡ ... ታዲያ "ነገርን ከመሰረቱ ..." እንዲሉ አበው፤ እስቲ በቅድሚያ እነ አቶ ኢሳያስን ወደ አበሳጨው ሁለተኛው የማዕቀብ እውነታዎች እንዝለቅ፡፡...

## የሃቆቹ መሠረቶች

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ከመሰንበቻው በከባድ የቤት ሥራ ተጠምዶ ነበር፡፡ የቤት ስራውም የተለመደው የአቶ ኢሳያስ አስተዳደር ጉዳይ ነው – በውግዘት ላይ ውግዘት፣ በማዕቀብ ላይ ማዕቀብ የማይሰለቸው ጉደኛ መንግስት። እናም የጸጥታው ምክር ቤት የኤርትራንና የሶማሊያን ጉዳይ እንዲያጠና የሰየመው አጣሪ ቡድንን 417 ገጾች ሪፖርት ደግሞ ደጋግሞ አገላበጠው፡፡ ... ግና ቢገለብጠውና ቢያገላብጠው አንዳችም ጠብ የሚል ነገር አላገኘበትም – የአስመራው አስተዳደር እኩይ ሴራ ዓይኑን አፍጦ፣ ጥርሱን አግጦ ፍንትው ብሎ ከመታየቱ በስተቀር አንዳችም 'እሰየው' የሚያስብል መልካም ነገር ሊገኝበት አልቻለም፡፡ በዚህ መነሻነትም የፀጥታው ምክር ቤት ሙሉ በሙሉ በሚባል መልኩ፤ ማዕቀብን እንደ ልዩ መገለጫና ኩራት የሚመለከተው የኤርትራ መንግስት ዳግም በዶቃ መልክ እንዲያንጠለጥለው ሰጥቶታል፡፡ ...

ታዲያ እዚህ ላይ 'የማዕቀቡ መሰረታዊ ሃቆች ምንድናቸው?' የሚል ጥያቄ ማንሳት ተገቢ ይመስለኛል፡፡ እንደሚታወቀው የአቶ ኢሳያስ አምባገነናዊ መንግስት በሀገሩ ውስጥ ከሚያከናውናቸው እጅግ ዘግናኝ እና እስከፊ የግፍ ተግባሮች ባሻገር፤ የጎረቤት ሀገራትን ሰላም ሲያደፈርስ የኖረ ሃይል ነው፡፡ እንደ አበደ ውሻ የሚያጎራብቱትን ሀገራት በሙሉ በሽብር ጥርሱ ነካክሷል፡፡ ከተጠናወተው ወታደራዊ ጀብደኝነት ተውሳክ በመነሳትም፤ ኮሽታ ስለሚያስደነግጠው ተገቢ ያልሆኑ ጦርነቶችን

ቀስቅሶ፣ ሰብዓዊና ቁሳዊ ኪሳራዎች እንዲደርሱ ማድረጉ ለፀጥታው ምክር ቤት አይረሴ ታሪክ ነው።

በዚህ ማንነቱ የሚታወቀው የኤርትራ መንግስት አል-ሸባብን ጨምሮ በርካታ ሽብርተኛ ቡድኖችን በፌታውራሪነት ከመምራቱም በላይ፣ ቋሚ የገንዘብና የህገ-ወጥ ጦር መሣሪያዎች ምንጭ ሆኖም በማገልገል ላይ ይገኛል፡፡ በቅርቡም በአዲስ አበባ የአፍሪካ ህብረትን 16ኛው የመሪዎች ልዩ ጉባዔን ለማደናቀፍ፣ ትክክለኛው የሽብር ቡድን የትኛው እንደሆነ እስከምንቸገር ድረስ የሚያምታታውን የኦነግ ቅጥረኞችን በመላክ ለማሸበር ያደረገው ሙከራ ሁነኛ አስረጅ መሆኑን የፀጥታው ምክር ቤት ተገንዝቧል፡፡

ከሶማሊያ ጋር አንድ ስንዝር እንኳን የድንበር ወሰን የሌለው የኤርትራ መንግስት፣ ላለፉት 20 ዓመታት በእርስ በርስ ጦርነት በምትታመሰው በዚያች ሀገር ውስጥ ዘልቆ በመግባት በእሳት ላይ ነዳጅ የማርከፍከፍ እሉታዊ ሚናውን ሲወጣ ቆይቷል፡፡ የምስራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግስታት ባለስልጣን (ኢጋድ) አባል ሀገራት ጉዳዩን ለፀጥታው ምክር ቤት "አቤት" ማለታቸው ትክክለኛ እና አግባብነት ያለው መሆኑን የተረዳው የፀጥታው ምክር ቤት፣ በአስመራው የሽብር ቡድን ላይ እርምጃ መወሰድ እንዳለበት በአጣሪ ቡድኑ ከቀረቡት ሃቆች ተረድቷል፡፡

ከዚህ ዕውነታ ተነስቶም ታህሣሥ 10 ቀን 2002 ዓ.ም በኤርትራ መንግስት ላይ የጦር መሣሪያ ማዕቀብ ጥሎበት ነበር፡፡ ሻዕቢያ ግን ዓለም አቀፍ ዕውቅና የተቸረውን የሶማሊያን የሽግግር መንግስት ከአሸባሪው አል-ሸባብ ጋር አብሮ ለመጣል በማሴሩ እንዲሁም ራስ ዱሜራ በተሰኘው የጁቡቲ ግዛት በኃይል ያስገባቸው ወታደሮቹን ለማስወጣት ፈቃደኛ ባለመሆኑ የመጀመሪያውን ማዕቀብ እንደጣለበት ያስታውሳል – የፀጥታው ምክር ቤት።

አሁንም ሃቁን ከአጣሪ ቡድኑ ሪፖርት በመነሳት ሲያጤነው፣ የአቶ ኢሳያስ መንግስት ነገር "ውኃ ቢወቅጡት እምቦጭ" እንዲሉት ዓይነት ሆኖ አግኝቶታል፡፡ በመሆኑም በሁለተኛው ማዕቀቡ በአቶ ኢሳያስ ሹማምንቶች ላይ የጉዞ እና የኢኮኖሚ እንዲሁም የጦር መሣሪያ ዝውውር ዕገዳ ጥሎባቸዋል፡፡ በዚህም ሃያ የማይሞሉ የህዝባዊ ግንባር ለዴሞክራሲና ለፍትህ (ህግደፍ) ቁንጮ አሸባሪዎችን የኤርትራን ህዝብ የማይጎዳ ማዕቀብን ዳግም አከናንቦታል፡፡

አንዳንድ ወገኖች የፀጥታው ምክር ቤት ማዕቀቡን በሚጥልበት ወቅት ቻይና እና ሩሲያ ድምጽ ተዓቅቦ ማድረጋቸውን ተከትሎ "ለምን?" የሚል ጥያቄ ሲያነሱ ይደመጣሉ፡፡ ይሁንና በእኔ እምነት እውነታውን የተረዱት አይመስለኝም፡፡ የቻይና አቋም በየትኛውም አቅጣጫ ሲፈተሽ በኤርትራ ላይ የተጣለውን ማዕቀብ ከመደገፍ ተለይቶ የሚታይ አይደለም፡፡ በእንዲህ ዓይነቱ የመጨረሻ በሆነ ድምጽን በድምጽ የመሻር መብት ወቅት ቻይና መታቀብን መምረጧ፤ በፖለቲካ ስሌት ሲታሰብ 'አዎ! ማዕቀቡን እደግፋለሁ' የማለት ያህል መሆኑን ለመገንዘብ አያዳግትም፡፡ በእርግጥ ሀገሪቱ በማዕቀቡ ላይ ተቃውሞ ቢኖራት ኖሮ 'አይሆንም!' የማለት መብት እያላት ዝምታን መምረጧ፤ የቀጣናው ውስብስብ ችግሮች ባለቤት የኤርትራ መንግስት መሆኑን በማወቋ እንደሆነ ለመረዳት ጥልቅ ጥናት ማካሄድ የሚያሻው ጉዳይ አይመስለኝም፡፡

የሩሲያም ሁኔታ ከዚህ የተለየ ነው ብሎ ማሰብ አይቻልም፡፡ ምክንያቱም ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደሞከርኩት፤ ይህች ሀገርም የኤርትራን መንግስት ማንነት ልክ እንደ ቻይና ጠንቅቃ ስለምታውቅ ነው፡፡ የወቅቱ የፀጥታው ምክር ቤት ሰብሳቢ የነበረችው ሩሲያ፤ የአቶ ኢሳያስ አስተዳደር "ከደሙ ንጽህ" ቢሆን ኖሮ እንደ ቻይና ድምጽን በድምጽ የመሻር መብት እያላት ስለምን መታቀብን መረጠች? ብለን ስጠይቅ፤ 'የአስመራው አስተዳደር ማንነት ወትሮውም ቢሆን አደባባይ ላይ ቆሞ ዕርቃኑን ፀሐይ እየሞቀ ነበር' የሚል ትክክለኛ ምላሽ ማግኘታችን አይቀርም፡፡ እናም ቻይናም ሆነ ሩሲያ በወቅቱ "ከባህሪያችን በመነሳት በማንም ሀገር ላይ ማዕቀብ እንዲጣል ባለመፍለጋችን ዝምታን መርጠናል" የማለታቸው ዲፕሎማሲያዊ ምላሽ ምስጢርም ይኸው ነው – 'ጉዳዩ እውነት ስለሆነ አንቃወምም' የሚል፡፡

ታዲያ ሃቁ ይህ ከሆነ ዘንዳ "የአስመራው ንጉስ" ከተንሳፈፉበት የእብሪት ፊኛ ወደ መሬት ወርደው ነባራዊ ሃቆችን መመልከት ከመመልከት ይልቅ፣ ጣታቸውን ለምን ወደ አጣሪ ቡድኑ ይቀስራሉ?' የሚል ጥያቄ ማንሳት ያስፈልጋል፡፡ እርግጥ ለጥያቄው ምላሽ ስንሻ፤ አቶ ኢሳያስ ዛሬም ድረስ ዓይናቸውን በጨው ታጥበው ባረጀ ያፈጀ የፕሮፓጋንዳ ፈረሳቸው ላይ ያለ ሃፍረት ተቀምጠው እናገኛቸዋለን፡፡ ዳሩ ግን እርሳቸው ምንም ይበሉ ምን፣ የአጣሪ ቡድኑ ማንነትና የተግባር ጥናቱ ቱባ ክንዋኔዎች ሲተረተሩ ይህን ይመስላሉ፡፡…

# አጣሪ ቡድኑ

እ.ኤ.አ መጋቢት 29 ቀን 2010 በጸደቀው የፀጥታው ምክር ቤት ውሳኔ ቁጥር 1916 (2010) አንቀጽ ስድስት ላይ የተሰጠውን ስልጣን፣ ተግባርና ኃላፊነት ይዞ የሚንቀሳቀሰው የሶማሊያና የኤርትራ ጉዳይ አጣሪ ቡድን፤ በአቶ ኢሳያስ መንግስት “ዓይኔን ግንባር ያድርገው” ድራማ “ሙያዊ ክሂሎት የሌለው፣ ገለልተኛ ያልሆነና በፈጠራ የተሞላ ሪፖርት ያቀረበ ...ወዘተ” የሚሉ አስገራሚ መከራከሪያዎች አይሏቸው ዘለፋዎች ቀርበውበታል፡፡

ግና “ጅራፍ ራሱ ገርፎ ራሱ የሎሣል” እንዲል የሀገራችን ሰው፤ ወትሮም የፈጸሟቸውን የግብረ-ሽበራ ተግባራት መለስ ብለው ከማየት ይልቅ ጣታቸውን ወደ ሌላው አካል የሚቀስሩትን የአስመራዎቹን የሽብር ባለሟሎች የለየለት ውሸት እንዲህ ዳግም ራቁቱን ማስቀረት ይቻላል፡፡ ... በቅድሚያ ግን ወደ ቡድኑ “ሙያዊ ክሂሎት” ብቃት ብናመራ ሳይሻል አይቀርም፡፡...

በመንግስታቱ ድርጅት የፀጥታው ምክር ቤት በቅርቡ ይፋ የሆነው ሪፖርት መገንዘብ እንደሚቻለው፤ የአጣሪ ቡድኑ አባላት ከሶማሊያና ከኤርትራ ጉዳይ ጋር ተያያዥ በሆኑ ጉዳዩች ዙሪያ ሙያዊ ክሂሎት ያላቸው ግለሰቦች ናቸው፡፡ የቡድኑ አስተባባሪ ማት ብራይደን በእንዲህ ዓይነት ዓለም አቀፍ ስራዎች የተካኑ መሆናቸው ግለ-ታሪካቸው ያወሳል፡፡ የሰብዓዊ ጉዳዮች ባለሙያዋ ካሮሊና ሪይስም በመንግስታቱ ድርጅት “አንቱ” የተሰኘ ስም ያላቸው ናቸው፡፡

የባህር ባለሙያው ጆርግ ሩፋሁት እንዲሁም የገንዘብ ጉዳዮች ባለሙያው ሚስተር ጋሳሃን ሳህብሎ በመንግስታቱ ድርጅት ብቃታቸው ታምኖበት የተሰየሙ ግለሰቦች ናቸው፡፡ ባባቱንዴ ታይዎ የተባሉት የታጣቂ ኃይሎች ባለሙያም ቢሆኑ በዚሁ መስፈርት መሰረት የጸጥታው ምክር ቤት ክሂሎታቸውን አምኖበት የመደባቸው ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም፤ የቡድኑ የተግባር እንቅስቃሴዎች አካል በመሆን የተሰበሰቡ መረጃዎችን በመገምገምና በማጠቃለያ ዘገባው ተሳታፊ የሆኑ በርካታ ግለሰቦች ስራውን በገለልተኝነት እንዲያግዙ ተደርጓል፡፡

ታዲያ እውነታው ይህ ከሆነ፤ “የአስመራው ንጉስ” አጣሪ ቡድኑን ምን እያሉት ነው? ኸረ ለመሆኑ ለእርሳቸው አንድ ግለሰብ ሳዋ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ገብቶ ካልሰጠነ አሊያም እንደ ኤርትራው “ኪሎማ” ዓይነት የአሸባሪዎች ማሰልጠኛ ካምፕ ገብቶ በሻዕቢያ የትርምስ ክሂሎት ተቀጣጣይ ፈንጂዎችን ተሸክሞ ካልተያዘ፤ ሙያዊ ብቃት የለውም ማለት ነውን? – እናንተዬ መቼም ነገሩን “ወቸው ጉድ!” እንጂ ከቶ ሌላ ምን ማለት ይቻላል? – በአቶ ኢሳያስ ቋንቋ “ክሂሎት ያለው ባለሙያ” ማለት እንደ አል-ሸባብ የንጹሃን ዜጎችን ደም በሚዘግንን ሁኔታ የሚያፈስ ቡድን ይሆን እንዴ?...

ዳሩ ግን የኤርትራው ፕሬዚዳንት ምንም ይበሉ ምን፣ አጣሪ ቡድኑ ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ያመነበተና ሙያዊ ክሂሎቱም የተመሰረከለት መሆኑን መገንዘቡ፤ የአስመራው አስተዳደር ቢያንስ ለዓለም አቀፉ ህግ ተገዥ እንዲሆን የሚያግዘው እንጂ የሚጎዳው አይደለም፡፡ ከዚህ ውጪ፤ “የራሷ እያረረባት፣ የሰውን ታማስላለች” እንዲሉ አበው፤ “ኢሳያሳዊያን” ዓይናቸው ውስጥ ያለውን ትልቅ የጥፋት ግንድ ማየት ተስኗቸው፣ በሌላው ወገን ዓይን ውስጥ የሌለን ጉድፍ ለማውጣት መሯሯጣቸው የማያዋጣቸው መሆኑን ሊያውቁት የሚገባ ይመስለኛል፡፡

አጣሪ ቡድኑ በኤርትራ መንግስት የተሰጠው ሌላኛው የዳቦ ስም “ገለልተኛ ያልሆነና በፈጠራ የተሞላ ሪፖርት ያቀረበ” የሚል አስገራሚ ውንጀላ ነው፡፡ እርግጥ ስለ ገለልተኛነትና ስለ ሪፖርት አቀራረብ ሰናወሳ፤ በቡድኑ ስራ ላይ የኤርትራ መንግስትን ሚና እንዲሁም የጥናቱን ዘዴዎች መመልከት የግድ ይለናል፡፡ የፀጥታው ምርክ ቤት የቡድኑ ሪፖርት ይፋ እንዳደረገው፤ የአስመራው አስተዳደር የቡድኑን የመረጃ አሰባሰብ ሂደት ለማደናቀፍ የራሱን ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡ ምክንያቱም ኤርትራ ውስጥ የመንግስታቱ ድርጅት ሰራተኞችና በሀገሪቱ የሚኖሩ ዲፕሎማቶችን ጨምሮ የውጭ ዜጎች እንቅስቃሴ የተገደበ በመሆኑ ነው፡፡ የሚዲያ ነጻነትና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችም ጉዳይ ሙሉ በሙሉ ዝግ ነው፡፡ ነገሩ “ምን ያለበት ዝላይ አይችልም” እንዲሉ በመሆኑ፤ የኤርትራ ባለስልጣናት ለቡድኑ መረጃ ለመስጠት ፈቃደኞች አልነበሩም፡፡

ይሁንና ቡድኑ ጥናቱ ፖለቲካዊ ድምጸት እንዳይኖረው በማሰብ፣ ከኤርትራ መንግስት ተቃዋሚ ኃይሎች አባላት አሊያም ከተቃዋሚ ቡድኖች ንኪኪ ካላቸው ግለሰቦች ጋር ለመገናኘት አልፈለገም፡፡ ይህን ያደረገውም ሪፖርቱ ገለልተኛና ተዓማኒ እንዲሆን በማሰብ ነው፡፡ ይሁንና የአቶ ኢሳያስ መንግስት በቀጣናው የሚያከናውነውን

የትርምስ አጀንዳ ስለሚያውቅ ለቡድኑ መረጃ አልሰጥም ብሎ ሲያበቃ፤ተመልሶ ቡድኑን በተለመደው ተራ የፕሮፓጋንዳ ምላሽ ለመወንጀል የፈለገው ሃቁን ለመሸፋፈን መሆኑ ከማንም የተሰወረ ጉዳይ አይመስለኝም፡፡ ሆኖም "እውነት ትመነምናለች እንጂ አትበጠስም" እንዲሉ አበው በቡድኑ ገለልተኛና በሳል ጥናት፤ የአስመራው መንግስት ከአል-ሸባብ ጋር ግንኙነት መመስረቱ፣ ለጽንፈኛ ቡድኑ ዕቅድ ማውጣቱ፣ ስልጠና መስጠቱ እንዲሁም ከሶማሊያ የፖለቲካ ሂደት ራሱን እንዳያገል መማጸኑና ለዚህም በየወሩ እስከ 80 ሺህ ዶላር የሚደርስ የገንዘብ ድጎማ ማድረጉ ተጋልጧል፡፡

ይህ ብቻ አይደለም፡፡ የኤርትራ መንግስት የፀጥታው ምክር ቤት ውሳኔ ቁጥር 1907 (2009)ን በመተላለፍ፤ የጂቡቲ፣ የኢትዮጵያ፣ የሱዳንና የኡጋንዳ ታጣቂ ተቃዋሚ ኃይሎችን እና አሸባሪዎችን በማሰልጠን፣ የገንዘብና የሎጀስቲክስ ድጋፍ ማድረጉ ተረጋግጧል፡፡ ይህ ተግባሩም ሻዕቢያ ኤርትራን ያህል ድሃ ሀገር ይዞ በቀጣናው የሚንቀሳቀሱ ጽንፈኞችን መርዳቱ የአስመራው አስተዳደር ብሎም የሀገሪቱን ገንዘብ ስርዓት በሌለው ሁኔታ መርጨቱ ለዜጎቹ ያለውን ደንታ ቢስነት የሚያሳይ ነው፡፡

እነዚህን አሳፋሪ ተግባራት በጉያው ውስጥ ሸጉጦ "ዓይኔን ግንባር ያድርገው" በማለት የአጣሪ ቡድኑን ስም ለማጥፋት የሚሯሯጠው የሻዕቢያው ቡድን፤ አንድ ጥናት የሚወሰነው በሚከተላቸው ዘዴዎች መሆኑን እንኳን ለማወቅ አይፈልግም፡፡ ይሁንና የአቶ ኢሳያስ ባለሚሎች ፈለጉም አልፈለጉም እኛ ግን አጣሪ ቡድኑ በጥናቱ ወቅት የተከተላቸውን ዘዴዎች መመልከታችን በጉዳዩ ላይ የጠራ ግንዛቤ እንድንይዝ ያደርገናል፡፡ በመጀመሪያው ደረጃ አጣሪ ቡድኑ የኤርትራንና የሶማሊያን ግንኙነት ለማጣራት የተጠቀማቸው ዘዴዎች ሳይንሳዊና ሙያዊ መሆናቸውን እንዲህ መመልከት ይቻላል፡፡

የፀጥታው ምክር ቤት ይፋ ያደረገው የቡድኑ ሪፖርት እንደሚያትተው፤ የጥናቱ መረጃዎች በሙሉ ከሁነቶችና ከርዕሰ ጉዳዮች ጋር የተነፃጸሩ ናቸው፡፡ ቡድኑ የተሰበሰቡ መረጃዎችን ጉዳዩ በሚመለከታቸው ባለሙያዎች በማስገምገም እንዲሁም ቡድኑ መረጃዎቹ ካላቸው ጠቀሜታና ከመረጃ ምንጮች ተዓማኒነት ጋር በማዛመድ እንዲጤኑ አድርጓል፡፡ ዘዴውን ከመረጃ ምንጭ ተዓማኒነት አኳያ ስንመለከተውም፤ ቡድኑ የመንግስት ባለስልጣናትን፣ የዲፕሎማሲያዊ ተልዕኮ ተወካዮችን፣ የሲቪል ማህበረሰብና የዕርዳታ ኤጀንሲዎችን ማነጋገሩ ትክክለኛ ሆኖ እናገኘለን፡፡ ሌላው ቀርቶ የጸጥታውን

ምክር ቤት ህግ የተላለፉ እንደ የኤርትራ መንግስት ዓይነት አካላትን በተዘዋዋሪ ለማግኘት ይቻል ዘንድ፤ ከእነዚህ ኃይሎች ጋር ቀጥተኛ ዕውቅና አሊያም በጉዳዩ ዙሪያ ቀጥተኛ መረጃ ያላቸውን ሰዎችን በታቀደና በተጠና መንገድ በማነጋገር ዕውነታውን ለማወቅ መጣሩ ምን ያህል ተዓማኒ መረጃን ለማግኘት ይጥር እንደነበር የሚያመላክት ነው፡፡

ይህ ብቻ እንዳይመስላችሁ፤ አቶ ኢሳያስ እንደለመዱት "ፈጠራ ነው" በማለት የገለጹት የቡድኑ ሪፖርት፤ እርሳቸው አስመራ ቁጭ ብለው ከሚፈበርኩት መረጃ በእያሌው የተለየ ነው፡፡ የቡድኑ አባላት እውነታውን ለማጣራት ቤልጅየም፣ ካናዳ፣ ጅቡቲ፣ ኤርትራ፣ ኢትዮጵያ፣ ፈረንሳይ፣ ጀርመን፣ ጣሊያን፣ ሊባኖስና ኔዘርላንድስ ድረስ አቅንቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ኖርዌይ፣ ኳታር፣ ሩማንያ፣ ሶማሊያ፣ ኡጋንዳ፣ የተባበሩት አረብ ኢሚሬትስ፣ እንግሊዝ፣ ሰሜን አየር ላንድ፣ ሰሜን አሜሪካና የመንን ያካለለ ጉዞ በማድረግ ትክክለኛው ሃቅ ላይ ለመድረስ ችሏል፡፡

እንግዲህ ከዚህ ዓይነት ሳይንሳዊና ሙያዊ ጥናት ውጪ፤ ገለልተኛ፣ ተዓማኒና ሃቅ ላይ የተመሰረተ ሪፖርት በማንና እንዴት ሊዘጋጅ እንደሚችል የሚያውቁት የኤርትራው ፈላጭ ቆራጭ መሪ ብቻ ናቸው፡፡ እርግጥም ለሻዕቢያው ቁንጮ "ትክክለኛ ሪፖርት" ማለት አስመራ አሊያም ምፅዋ ቤተ-መንግስቶች ውስጥ ሽበጥ ተጫምቶና ሁለት እግርን አነባብሮ ቁጭ ተብሎ የተፈበረከና ሃያ በማይሞሉት የሀገሪቱ የሽብር አጋፋሪዎች የተቀነባበረ ሊሆን ይችላል፡፡ ይሁንና ይህን መሰሉ የቅጥፈት ፕሮፓጋንዳ አቶ ኢሳያስ እንደ ተረኛ ዜና አንባቢ በየዕለቱ በሚደሰኩሩበት የኤርትራ ቴሌቪዢን እና "አንድ ለእናቱ" እየተባለ በሚጠራው "ሃዳስ ኤርትራ" ጋዜጣ ላይ እንጂ፤ በዓለም አቀፉ ማህብረሰብ ፊት መሳቂያና መሳለቂያ ከመሆን የማይዘል መሆኑን እነ"እያ ነውጤ" መገንዘብ ያለባቸው ይመስለኛል፡፡ ለምን ቢባል፤ የኤርትራ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ሰሞኑን "ገለልተኛ ያልሆነው አጣሪ ቡድን ይቀየርልኝ" በሚል ለፀጥታው ምክር ቤት የጻፈው ደብዳቤ፤ "ዶሮን ሲያታልሏት፣ በመጫኛ ጣሏት" እንዲሉት ዓይነት መሆኑን ዓለም ስለሚያውቀው ነው፡፡ ታዲያ አቶ ኢሳያስ አጣሪ ቡድኑን ምን አድርግ እያሉት ይሆን?...

## “የአብዬን ወደ እምዬ”

የአስመራው መንግስት በአጣሪ ቡድኑ ላይ ጣቱን የቀሰረው እጅግ በሚያስገርም፣ ምንም ዓይነት ተጨባጭ እውነታ በሌለውና መሰረተ-ቢስ በሆነ ተራ ውሸት ነው፡፡ ይኸውም “የቡድኑ ሪፖርት የአሜሪካንና የኢትዮጵያን መንግስታት ፍላጎት ለማሟላት” የሚልና የራስን የቆየና ከደም ጋር የተዋሃደ ችግሩን በሌላው ላይ የማላከክ አባዜው መሆኑን ብእርግጠኝነት መናገር ስለሚቻል ነው፡፡

እንደ እውነቱ ከሆነ ይህ የኤርትራ መንግስት ያለ አቅም የመንጠራራት አባዜ ከማንነቱ ጋር የተቆራኘ በሽታ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ትንሹ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ በአፋኝነቱና በጸረ-ህዝብነቱ የሚታወቀው የአቶ ኢሳያስ አስተዳደር፤ በየትኛውም መስፈርት ከማይገናኛቸው አሜሪካና ኢትዮጵያ ጋር ራሱን በህልም ዓለም መነጽር እየተመላከተ ለማወዳደር መሞከሩ ከበሽታ ውጪ ሌላ ስያሜ ሊያሰጠው የሚችል አይደለም፡፡ ሆኖም የኤርትራ መንግስት በሌለ ማንነቱ ራሱን ከተፈጠረበት የሳህል ተራራ እኩል ቆልሎ በማየት፤ በገዛ እጁ በሚፈጥራቸው ችግሮች አሉባልታን እየደሰኮረ እና “የአብዬን ወደ እምዬ” እንዲሉት ዓይነት ፈጠራን እየቀመረ የሚያቀርባቸው ማደናገሪያዎች ነጻ እንደማያውጡት መገንዘብ ያለበት ይመስለኛል፡፡

በዚህ ጽሑፍ አቅራቢ እምነት፣ ይህ የኤርትራ መንግስት አጉል የመንጠራራት ትምክህት በሽታን የመደበቅ አካሄድ ነው፡፡ ዳሩ ግን “ህመሙን የሚደብቅ ፈውስ አይገኝለትም” እንዲሉ አበው፤ የዚያች ሀገር ቱባ ባለስልጣናት ከህመማቸው ለመፈወስ ለእነርሱ የማይታያቸውን “ዕርቃናዊ ማንነት” በግልጽ ማየት ይኖርባቸዋል። ለዚህም በአሁኑ ወቅት በውስጣቸው ያሉትን፣ ነገር ግን እውነታዎችን ለመገንዘብ የሚያግዟቸውን የሰብዓዊነት መመዘኛዎችን መለስ ብለው መቃኘት አለባቸው፡፡ ታዲያ ለዚህ ጽሑፍ አንባቢያን ይህ ሃቅ ግልጽ ይሆን ዘንድ፤ የሻዕቢያን በሽታ በውል ማወቅ ይኖርብናል፡፡ እርግጥም ነገሩ ወዲህ ነው፡፡…

የኤርትራ መንግስት ጥቂት አመራሮች እጅግ በተሳሳተ የ”ታላቅነት” አባዜ ውስጥ እየዳከሩ ነው፡፡ በዓለም አቀፍ መድረኮች የአንዲት ትንሽ፣ ከተመሰረተች ሁለት አስርታትን በቅርቡ የዘለለችና በጦርነት የተጎዳች ድሃ ሀገር መሪዎች መሆናቸውን እንኳን ዘንግተውታል፡፡ ከልዕለ ኃያሏ አሜሪካ ጋር በእኩል ስሜት ጎን ለጎን ይፎካከራሉ። በምጣኔ

ሀብት፣ በዴሞክራሲና በዲፕሎማሲው ረገድ፣ ልክ የዔሊና የጥንቸል ዓይነት ርቀት ከምትቀድማት ኢትዮጵያ ጋርም ያለ ሃፍረት ራሳቸውን  ይለካሉ፡፡ ታዲያ ለእንዲህ ዓይነቱ ህመም ምንም ዓይነት ፖለቲካዊም ይሁን ዲፕሎማሲያዊ ህክምና ሊኖር አይችልም፡፡ እናም ከህመሙ ለመፈወስ ቀላሉ መንገድ በቅርብ ወደሚገኝ የሥነ-አዕምሮ ህክምና ክፍል  ማምራት ብቻ ነው፡፡

ምንም እንኳን የአስመራው አስተዳደር አምባገነን አመራሮች የበሽታቸውን መንስዔ ለማወቅ ባይሹም፤ ራሳቸው በራሳቸው ከፈጠሩት ህመም ለመፈወስ ከፈለጉ መድሃኒቱ ያለው በእጃቸው ነው፡፡ ችግራቸው ከሌሎች ሀገሮች የተላከባቸው ልክፍት ወይም ወረርሽኝ አይደለም፡፡ የእነ አቶ ኢሳያስን ህመም አሜሪካ፣ ኢትዮጵያ አሊያም ተመድ አልፈበረኩትም – ራሳቸው በራሳቸው ችግሮችን ፈጥረው አጀንዳቸውን ዘርግተዋል እንጂ፡፡ ስለሆነም በ“የአብዬን ወደ እምዬ” የተሳሳተ ብሂል በሌሎች ወገኖች ላይ የቁራ ጩኸት የሆነን አሉባልታ እየነዙ መኖር ከቶም መፍትሄ ሊሆን እንደማይችል መረዳት  አላባቸው ባይ ነኝ፡፡

## ማጠቃለያ

በአሁኑ ወቅት የኤርትራው የአምባገነኖች ቁንጮ የራሳቸውን ችግር ከማረቅ ይልቅ፣ ሌሎችን በምክንያትነት የሚያቀርቡትን “ጨዋታ”፤ቀደም ባሉት ጊዜያት “በአምገነኖች ሊግ” ውስጥ የነበሩ መሪዎችም ተጫውተውታል፡፡ ይሁንና “ጨዋታውን” የሊጉ ግንባር ቀደም ተሰላፊዎች የነበሩት የኡጋንዳው ኤዲ አሚን ዳዳ፣ የግብፁ ሆስኒ መባረክ፣ የሊቢያው ሙአመር ጋዳፊ ወዘተ. በሚገባ ተጫውተውት በፎርፌ ለመሸነፍ በቅተዋል፡፡ አቶ ኢሳያስ ግን ከዚህ ዓለም አቀፍ እውነታ ለመማር ፈቃደኛ አደይሉም፡፡ ሆኖም የሥርዓታቸው ዋነኛ ገፈት ቀማሽ የሆነው የኤርትራ ህዝብ አምባገነኖችን ከጫንቃው  ላይ አሽቀንጥሮ የሚጥልበት ጊዜ ሩቅ አይመስለኝም፡፡

እርግጥ የአገዛዙ ሰለባ ከሆኑት ከዚያች ሀገር ህዝቦች ወዲያ የአቶ ኢሳያስን አምባገነናዊ ሥርዓት የሚገረስስ ኃይል አይኖርም፡፡ ምክንያቱም እርሱን ተክቶ ሊታገልላቸው የሚችል አካል ሊኖር ስለማይችል ነው፡፡ እናም የሻዕቢያን በባዶ ጉራ የተገነባ “ላም አለኝ በሰማይ፣ …” ዓይነት ተራ ፕሮፓጋንዳ ወደ ጎን ገሸሽ አድርገው ራሳቸውን ከአንድ ሰው አገዛዝ ማላቀቅ ይጠበቅባቸዋል፡፡ የሀገራቸው አምባገነኖች ራሳቸው

በፈጠሯቸው ችግሮች ሳቢያ ጭንቀት  ሲይዛቸው የፀጥታው ምክር ቤት የሰየመውን አጣሪ ቡድን እና ሌሎች ሀገራትን በማውገዝ የሚያነበንቡትን ቅጥፈት ከግምት ውስጥ ባለማስገባት እንዲሁም በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚሰጡ ውሳኔዎች በአሁኑ ወቅት የጀመሩበትን ትግል እንደሚያጠናክርላቸው በመገንዘብ የራሳቸውን  ዕድል በራሳቸው የሚወስኑበት ጊዜ አሁን ይመስለኛል፡፡

የኤርትራው መንግስት በዓለም አቀፉ ማህብረሰብ ፊት ሀገራቸውን የሃፍረት ሻማ ያከናነበ በመሆኑም፣ በእንዲህ  ዓይነት "የሽብርተኞች አቀንቃኝ" ተብሎ  በተሰየመ ቡድን ዜጎች መመራት ያለባቸው አይመስለኝም፡፡ ሌላው ቀርቶ ከተመሰረተች ገና አንድ ዓመት ያልሞላት ደቡብ ሱዳን እንኳን የአጣሪ ቡድኑን ሪፖርት ትክክለኛነት በማረጋገጥ፣ የፀጥታውን ምክር ቤት የማዕቀብ ውሳኔን  መደገፏ የታሪክ ጠባሳ መሆኑን መገንዘብ ይኖርባቸል፡፡

አንድ 21 ዓመታትን ያስቆጠረ ነጻ ሀገር፣  ከተመሰረተ ሁለት መንፈቆችን እንኳን ባልሞላው ሀገር መብጠልጠሉ የቡድኑን ጥናት ትክክለኛነት እንጂ፣ ሻዕቢያ በጭንቀት ተውጦ  የሚያመርታቸውን  ውሸቶች የሚያመላክት አለመሆኑን ሊረዱ ይገባል፡፡ እናም የፀጥታው ምክር ቤት ዳግማዊ የማዕቀብ ውሳኔ ገቢራዊ ማድረግ ማለት፣ ለጭቁኖቹ ኤርትራዊያን መንታ ምላሽን ያዘለ ወርቃማ ተግባር ነው – አንድም በህዝቡ አንጡራ ሀብት የሚንደላቀቁትን የአስመራዎቹን አምባገነኖች ያሽመደምዳል፣ ሁለትም ወንድም የሆነውን የዚያች ሀገር ህዝብ ከአፈናና  ባርነት ነጻ ያወጣል፡፡ እናም የዚያች ሀገር ዜጎች እነ አቶ ኢሳያስ  በአጣሪ ቡድኑም ላይ ይሁን በሌሎች ሀገሮች  ላይ የሚለጥፉት የቀቢጸ-ተስፋ "ታፔላ"፣ ከፃዕረ-ሞት ጋር የሚያደርጉት ትንቅንቅ መሆኑን በማወቅ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ድጋፍ የሚያደርጉበት ቀን አሁን ይመስለኛል፡፡ ቸር እንሰንብት፡፡